**የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)**

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


# በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የተካሄደውን ድብደባና እስራት እናወግዛለን

ህዳር 27፣ 2007

ዛሬ ቅዳሜ ህዳር 27 ቀን 2007 ዓ. ም (ዲሴምበር 6፣ 2014) በዘጠኝ ተቃዋሚ ድርጅቶች አስተባባሪነት በአዲስ አበባ ተጠርቶ በነበረው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የህወሀት/ኢህአዴግ አገዛዝ የጸጥታ ሰራዊት ህዝቡን በዱላ በመደብደብና ብዙዎችን ወደ እስር በመወርወር ሰላማዊ ሰልፉን በትኗል። የዚህ ግፍ ሰለባ ከሆኑት ውስጥም የትብብሩ ሰባሳቢ ኢንጅነር ይልቃል እነደሚገኙበት ታውቋል። ይህን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ሸንጎው አጥብቆ ያወግዛል። በግፍ የታሰሩት ሁሉ ባስቸኳይ እንዲፈቱም ይጠይቃል።

የህወሀት/ኢህአዴግ ስርአት ህዝብን ሰጥ ለጥ አድርጎ፣ በግፍ አስፈራርቶና አፍኖ ለመግዛት ቢጥርም፣ ወደ አደባባይ የወጡ ዜጎች ጀግንነት ደግሞ ለመብት መከበር የሚደረገው ሰላማዊ ትግል በማያቋርጥ ሁኔታ ድፍረትን እያገኘ፣ ጥንካሬን እየተጎናጸፈ እንደሆነ ያመላክታል። ከዚህም በተጨማሪ በዛሬው እለት በሰላማዊ ሰልፍ ላይ የተሳተፉትን ወገኖቻችንን ስንመለከትም ትግሉ አያደር ወጣቱን እያሳተፈ፤ በብሄር፣ በሀይማኖት በጾታና በእድሜ ስብጥሩም እየሰፋ እንደሄደ ያሳየናል። ይህ በቀጣይነት እየተካሄደ ያለው ሕዝባዊ ትግል መበረታታትና መደገፍ ይገባዋል።

ህዝብ በስርአቱ ላይ ያለው ተቃውሞ፣ አግዛዙ በሀገራችንና በዜጎቻችን ላይ በተከታታይ በሚፈጽማቸው ግፎች ምክንያት ነው። የተቃውሞው መሰረት ለ23 አመታት በተለያየ ወቅት የተደረገው የሀገር ድንበር የመሸራረፍ ወንጀልና በቀጣይ የፈጠረው ብሄራዊ ውርደት፣ ተግባራዊ እየሆነ ያለው ህዝብን እርስበርስ የሚያጋጭ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ፤ የመሰረታዊ መብቶች አፈና፣ በነጻ የመደራጀት መብት መከልከል፣ የፍትህ መጥፋት፣ እስራት፣ ግርፋት፣ የንብረት ነጠቃ፣ የድህነት መስፋፋት፣ መፈናቀል፣ ረሀብ እርዛት…ወዘተ ናቸው።

ይህ ግፍ፤ እስራት፤ አፈና፤ ድብደባና ግድያ እስካላበቃና የሕግ የበላይነትና የሕዝብ መሠረታዊ መብቶች እስካልተከበሩ ድረስ፤ የህዝብን ተቃውሞ በፕሮፓጋንዳ ብዛት፣ በዱላና በማስፈራራት…ወዘተ ለማስቆም ከቶውንም አይቻልም። አስተዋይ ለሆነ ሰው በተለያዩ ሀገሮች የተካሄደውን ያምባገነኖች መጨረሻ በማገናዘብ ትምህርት ሊወሰድ ይገባዋል። ለሰላሳና ለአርባ አመታት ባምባገነንነት ህዝብን ይረግጡ የነበሩት እነ ሆስን ሙባረክ፣ ሙአመር ጋዳፊና ሌሎችም የዘረጉት የስለላና የፕሮፓጋንዳ መዋቅር ከህዝብ ቁጣ ሊያድናቸው እንዳልቻለ የሚታወቅ ነው። የሁለቱም አምባገነኖች መጨረሻቸው በውርደት መሞት ወይም ወደ እስር መወርወር ነበር የሆነው።

የህወሐት/ኢህአዴግ መሪወችም ዛሬም ከዚህ ከገቡበት የቅዠት አለም፣ ራሳቸውን አላቀው ከአጥፍቶ የመጥፋት እርምጃ ሊላቀቁ ይገባቸዋል። በተለያየ ምክንያት ይህን ስርአት የሚያገለግሉ ሁሉ የዚህ ግፍ መሳሪያ ሆኖ መቀጠል ከቶውንም እንደማይገባ ሊገነዘቡም ይገባል። ዛሬ ስርአቱን ትብብር መንፈግና፣

በቃኝ ማለት ከሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ታሪካዊም ሀገራዊም ግዴታ ነው። እያንዳንዱ ግለሰብ ነገና ከነገ ወዲያ ከሚያስጠይቅ የግፍ ተግባር ራሱን ማራቅና ከህዝብ ጎን መሰለፍ ጊዜው የሚጠብቀው ሃላፊነት ነው።

ዛሬ እያደገ የመጣው የህዝብ ትግል ተጠናክሮ የሚፈለገው የስርአት ለውጥ እውን እንዲሆን ደግሞ፣ ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች ከባእድ ተጽእኖ ነጻ ሆነው  ቢቻል በአንድነት ባይቻል ደግሞ በመተባበር ትግሉን ወደፊት ለማራመድ መስራት ይኖርባቸዋል።  ሰላማዊ ሰላፎችን በጋራ ወይም በመደጋገፍ ማካሄድ አንዱ የትግሉ ገጽታ  ነው።

የህዝብ ትግልም በዋናነት በሀገር ውስጥ የሚከናወን ስለሆነ ትግሉን ለማጠናከር ደግሞ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትግሉ አጋዥ መሆን ብቻ ሳይሆን የትግሉ ባለቤት መሆንም ይኖርበታል። ይህን ለማድረግም አንዱ ድርጅት በሚጠራው ሰልፍ ላይ የሁሉም ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች እንዲሳተፉ ማበረታታትና ማስተባበር አስፈላጊ ይሆናል።  የእያንዳንዱ ላንድነትና ለፍትህ የቆመ ሀይል እንቅስቃሴ ስኬታማነት ለሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች መጠናከርና መጎልበት አጋዥ ነው።

በዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) በሀገር ቤት ትግላቸውን በሰላማዊ መንገድ በማካሄድ ላይ ለሚገኙት፣ የዘጠኙን ድርጅቶች ትብበብር፣ ለአንድነት ፓርቲ፣ ለመኢአድና ለመድረክ ያለውን የትግል አጋርነት እየገለጸ በሚያካሂዱትም ሰላማዊ ትግል ከጎናቸው እንደሚቆም እንደሁልጊዜው አሁንም ያረጋግጣል።

በዚህ አኳያም፣ የህዝቡን ትግል የሚሻውን ፖለቲካዊ አመራር ለመስጠትና የህዝብን ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት ለመግፋት ግዜው የሚጠይቀውን አጣዳፊ ጥሪ በመገንዘብ ቢቻል በህብረት ለመስራት ባይቻል ደግሞ በሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ ለመተባባር ጥረታችውን እንዲያጠናክሩ ጥሪያችንን በድጋሚ እናቀርባለን፡

የአንድነት ኃይሉ የተባበረ ትግል የድሉ ዋስትና ነው!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790  E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**